# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 303 የካቲት 21 2006 ገጽ 1


ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህም በፊትም ደጋግሞ እንደገለጸው፤ በተለያዩ ጊዜያት ራሳቸውን ከወያኔ ባርነት ነፃ ለማውጣት በወሰዱት እርምጃ መስዋእትነት የከፈሉ የብአዴን አባላት መኖራቸውን ያውቃል። ግንቦት 7 ለእነዚህ ቆራጦች ትልቅ አክብሮት አለው። ዛሬም ህሊናቸውን ሙሉ በሙሉ ያልሸጡ የብአዴን አባላት አሉ ብሎ ያምናል። እነዚህ ወገኖቻችን ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የግል፣ የወገንና የአገር ግዴታ አለባቸው ብሎ ያምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር ይሻላል - የባህር ዳሩ ሰላማዊ ሰልፍ መሪ ቃል ነበር!

አንድነት እና መኢአድ ባዘጋጁት ሰልፍ ላይ ከተሰሙ መፈክሮች ጥቂቶቹ ሲሆኑ፥ የሃሩሩ ፀሃይ ሳይበግራቸው በርካታ ሰልፈኞች በባዶ እግራቸው በመሆን በገዢው ብአዴን ላይ ያላቸውን ከፍተኛ ቁጣ አሰምተዋል። በሰላማዊ ሰልፉ ከታዘለ ሕጻን ጀምሮ እስከ አዛውንቶች የተሳተፉበት እና የወጣቱ ተሳትፎ የጎላበት ሲሆን ወጣቱ ክፍል ሆ ብሎ በነቂስ በመውጣት እልህና ወኔ በተሞላበት ትእይንት ማንነቱን በገሀድ ያስመሰከረበት እንደነበር በርካቶች ምስክርነታቸውን እየሰጡ ይገኛሉ፡ ወጣቱ በአደገኛ ሱሶች በመጠመዱ ለመብቱ መቼውንም አይነሳም እየተባለ በወያኔና ቱልቱላ ካድሬዎቹ ሲሚረትበት የነበረው ከሚርትነት ያለፈ አለመሆኑን በተግባር አስመስክሯል። በዕለቱ ሠልፈኞቹ ካነገቧቸዉ መፍክሮች ዉስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።-

- ብአዴን የአማራን ህዝብ ለመምራት የሞራል ልዕልና የለውም! እምቢ ለአምባገነኖች!
- ክብራችንን የደፈሩት የብአዴን አባላት ለፍርድ ይቅረቡ! ነፃነታችን በእጃችን ነው!
- መተማ የኛ ነው፣ ቋራ የኛ ነው! ህዝብን እያዋረዱ መግዛት አይቻልም!

በሰልፍ ላይ የፋሽስቱ ወያኔ አሽከር አለምነው መኮንን በአማራ ህዝብ ላይ የተናገረው የጥላቻ ንግግር በምንታርቦ ለሰልፈኛው የተለቀቀል ሲሆን፤ ሰልፈኛውም በቁጭት በጉጅሌው ወያኔ የጥፋት ክንፍ በሆነው ብአዴን ላይ ተቃውሞውን አሰምቷል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የፓይለት ሃይለመድህን አበራ እናት አራጣ አበዳሪዎች ናቸዉ ተብሎ የተነገረዉን አሉባልታ አስተበ አበሉ

የኢትዮጵያዊው ረዳት ፓይለት ሃይለመድህን አበራ ጉዳይ አሁንም ድረስ አነጋጋሪነቱ እንደቀጠለ ነው። በበርካቶች ዘንድ ፖለቲካዊ አንድምታ እየተሰጠው የሚገኘው ይህ ክስተትንን በመደገፍ በተለያዩ የአለም ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያን ከሃይለመድህን አበራ ጐን በመቆም የድጋፍ ሰልፍ በማድረግ ላይ እንደሆኑ ምንጮቻችን አድረሰውናል።

በተያያዘ ዜና የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኞች በረዳት ፓይለት ሃይለመድህን አበራ ቤተሰብ ላይ ከፍተኛ ጫና እያደረሱ ሲሆን፡ አዛውንት የሆኑት እናት እና አባቱ ላይ ከሚደርስ መሰረት የለሽ ውንጀላን ጨምሮ እየደወሉ ማስፈራራት፡ በሃገር ቤት ያሉ መላ ቤተሰቦቹ ምንም አይነት መግለጫ እንዳይሰጡ እስከመከልከል፡ መዛት፡ ማስፈራራትና የመሳሰሉት ወያኔያዊ ሽብሮች እየደረሱባቸው መሆኑ ተሰምቷል።

ፋሽስቱ ወያኔ ቤተሰቡን በማስፈራራትና መጠቀሚያ ለማድረግ በአራጣ አበዳሪነት ለመወንጀል እያደረገ ያለውን መሰረት የለሽ ክስ ያስተባባሉት የሃይለመድህን ወላጅ እናት ወ/ሮ የዝባለም ስዬም ባለቤታቸው መንግስት ያውቀው ነጋዴ መሆኑን በመናገር፡ አሁን ለደረሰብን ችግር ማስፈራሪያ የዱርየዎች ዛቻ እንጂ እኛ አራጣ አበዳሪ አደለንም፡ አራጣ ማበደርም ወንጀል መሆኑን ጠንቅቀን እናውቃለን ሲሉ፡ በጉጅሌው ወያኔ እየደረሰባቸው ስላለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ምላሽ ሰጥተዋል።

አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ምሁር ለሬዲዮ ክፍላችን እንዳደረሱን፡ ረዳት ፓይለት ሃይለ መድህን አበራን በመደገፍ በአለም እየተደረጉ ያሉ ሰልፎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው በመጠቆም የወያኔው መንግስት ጨንቆት የሚለው ባጣበት እና በፈጠራ ወንጀል ድራማ ለመስራት በሚኳትንበት በዚህ ጊዜ እውነታውን ለአለማቀፉ ማህበረሰብ ለማስረዳት የእያንዳንዳችን ጥረት ወሳኝነት እንዳለው በማመን ለሕዝቦች የመብት ትግል የሚከፈሉ መስዋትነቶች እንዳይዳፈኑ አጥብቀን መታገል ይኖርብናል፡ ከረዳት ፓይለት ሃይለመድህን አበራ ጐን በመሰለፍም ወያኔን ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ብአዴን የባህርዳሩ ሠልፍ እንዳይሳካ ለማድረግ የጣረዉ ጥረት መና ቀረ

አለምነው መኮንን የአማራን ህዝብ መዝለፉን ተከትሎ ህዝቡ ቁጣዉን እንዲገልጽ አንድነት ፓርቲና መኢአድ የጠሩተን ሰልፍ ለማደናቀፍና ህዝብ በሰልፉ ላይ እንዳይገኝ ብአዴን የተቀየሰው ስትራቴጂ ሳይሳካ መቅረቱን የሰልፉ አዘጋጆች ለዝግጅት ልፍላችን በላኩት መልዕክት ገለጹ። የደህንነት ሰራተኞችንና የተለያዩ የፖሊስ ኮማንደሮችን ከአዲስ አበባ ባህር ዳር ድረስ በማጓጓዝ በህዝቡና በሠልፉ አአጋጆች ላይ የስነ ልቦና ጫና ለመፍጠር ያለሰለሰ ሙከራ ቢደረግም ህዝቡ የፌደራልና የክልል ፖሊሶችን ጋጋታ ከምንም ሳይቆጥር በነቂስ ወጥቶ ቁጣዉን በወያኔና በባዕዴን ላይ ሲገልጽ ዉሏል።

በተቃውሞው ማግስት ብአዴን ነባር አመራሮችን በአስቸኳይ ወደ ባህርዳር በመጥራት ዝግ ስብሰባ እያካሄደ ነው። ንቅናቄው እስካሁን ድረስ በሰልፉ ዙሪያ ወይም በአቶ አለምነው ንግግር ላይ የአቋም መግለጫ አላወጣም።በባህርዳር የተካሄደው ሰልፍ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃት መፍጠሩንም ዘጋቢያችን ገልጻለች። አንዳንድ የብአዴን አባላት ሳይቀሩ ህዝቡ ባሳየው ተሳትፎ ከሁሉም በላይ ስለነጻነቱ፣ ስለ ኢኮኖሚውና ፍትህ አንግቦ የተነሳው ተቃውሞ እንዳስደሰታቸው ለዘጋቢያችን ገልጸውላታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ አለምነው መኮንን የአቶ መለስ ዜናዊ ጭፍን አምላኪ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ጓዶቻቸው ለኢሳት ተናግረዋል። አቶ አለምነው በባህርዳሩ ስብሰባ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ብቸኛ የርእዮት አለም ሰው መለስ ዜናዊ እንደነበርና ሌላው ሁሉ ተከታይ መሆኑን መናገራቸው የአቶ መለስ ፍልስፍና አራማጅ መሆናቸውን እንደሚያሳይ ገልጸዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የወያኔን የሰብአዊ መብቶች ረገጣ አወገዘ

የአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በየአመቱ በአለም ዙሪያ የሚገኙ መንግስታትን የሰብአዊ መብት አያያዝ አስመልክቶ ከሚያወጣቸዉ አመታዊ ሪፖርቶች አንዱ በሆነዉ በ2013 ዓም ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽንና የመደራጀት መብቶችን በመርገጥ ቀዳሚዋ የአፍሪካ አገር አንደሆነች አስታወቀ። ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ አገዛዙ በየቀኑ የሚፈጽማቸዉን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን ከዝርዝሮቹ ውስጥ ሃሳብን በነጻነት የመግልጽና የመደራጀት መብት ቀዳሚ መሆናቸዉን ሪፖርቱ ይገልጻል።

ዜጎች በዘፈቀደ ይታሰራሉ፣ ይታፈናሉ፣ በእስር ቤት ይሰቃያሉ፣ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ይገደላሉ፣ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል እንዲሁም በእስር ቤት ውስጥ አሰቃቂ ድርጊቶች ይፈመግልጽናጸሙባቸዋል። ፍርድ ቤቶች በመዳከማቸው የፖለቲካ ፍለጎት ማስፈጸሚያ መሳሪያ መሆናቸውን፣ ዜጎች መንግስትን የመለወጥ እድላቸው አነስተኛ መሆኑን፣ ፖሊስ፣ አስተዳደርና ፍርድ ቤቶች በሙስና የተዘፈቁ በመሆናቸው ተጠያቂነት ያለበት ስርአት ማስፈን አለመቻሉን ሪፖርቱ ያስረዳል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የኦሮምያ ክልል አለማየሁ አቶምሳን ለመተካት በሚደረገዉ ሽኩቻ እየታመሰ ነዉ

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የሚል ሹመት ከተሰጠዉ ቀን ጀምሮ ኑሮዉን አገር ዉስጥና ካገር ዉጭ ባሉ ሆስፕታሎች ዉስጥ ያደረገዉ አለማየሁ አቶምሳ ባለፈዉ ሳምንት የክልሉ ምክር ቤት ሳያቀውቀው በስራ አስፈጻሚው እውቅና ብቻ ከስልጣን ከተነሳ በኋላ እሱን ለመተካት የሚደረገዉ የርስ በርስ ሽኩቻ ኦህዴድን ለሁለት ከፍሎ እያወዛገበ መሆኑን ከክልሉ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። የዛሬ ሦስት አመት ሳይታሰብ አባዱላ ገመዳን ፈንቅሎ ወደ ስልጣን የመጣዉ አቶ አለማየሁ አቶምሳ አባዱላንና ተከታዮቹን በመምታት ከስልጣን ውጭ እንዳደረጋቸዉ የሚታወቅ ሲሆን፣ በአሁኑ ግዜ አባ ዱላ ገመዳ ይህህ አጋጣሚ በመጠቀም ተመልሶ ወደ ቀድሞዉ ቦታ ለመመልስ ሽንጡን ገትሮ እየሰራ ነው።

እስካሁን ድረስ የክልሉ ምክር ቤት ስበሰባ አለመጠራቱም ታውቋል። አንዳንዶች እንደሚናገሩት ህወሃት ለዘብተኛ የሆነ መሪ እንዲመጣ ፍላጎት በሚያሳየው ፍላጎት የሁለቱም ሰዎች ደጋፊዎች ላይሾሙ ይችላሉ ። አቶ አለማየሁ የመሰረቱት አስተዳደር በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙትን መለስተኛ ከተሞችን ለመስተዳድሩ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የ10 በ90 ፕሮጀክት እንዲደናቀፍ ማድረጋቸውን በማንሳት እርሳቸውን የሚተካው ሰው ለዘብተኛ ሆኖ ከፌደራል ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር ይሻላል!!!

የባህርዳር እና አካባቢው ሕዝብ ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር ሺህ ጊዜ እንደሚሻል አካሉን ብቻ ሳይሆን ህሊናውንም ለትግራዩ ነፃ አውጪ ህወሓት ባርነት ላስገዛው "የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)" እያለ እራሱን ለሚጠራው ድርጅት መሪዎች ተናገረ።

ባርነት ክፉ ነው። በባርነት ላይ የጭንቅላት ባዶነት ሲታከልበት ደግሞ አለምነው መኮንንን የመሰሉ የብአዴን መሪዎችን ይፈጥራል። የብአዴን መሪዎች ለጌታቸው ህወሓት ያላቸውን ታማኝነት ለማሳየት ራሳቸውን ማዋረዳቸው ሳያንስ እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ በጅምላ መስደባቸው ብአዴን እንደ ድርጅት የሚገኝበት የተዋረደ ደረጃ ያሳያል።

ህሊና ያለው ባርያ ዛሬ ነፃ ባይሆንም ወደፊት ነፃ የመውጣት ህልም አለው። ዛሬ በጉልበተኛ የባርያ አሳዳሪ ነፃነቱን ቢያጣም የህሊና ነፃነቱን ያላስደፈረ ባርያ ለነፃነት መታገሉ የማይቀር ነው። እንደ ብአዴን መሪዎች በታማኝ ባርያነቱ እየፈነጠዘ ያለ ባርያ ግን ነፃ ሰው የመሆን ህልሙንም ጭምር አጥቷል። እንዲህ ዓይነቱ ባርያ በአካልም፤ በመንፈስም ባሪያ ነው። ነፃ ሰው የመሆን እድል የለውም።

የአማራ ሕዝብ ብአዴንን የመሰለ አሳፋሪ ድርጅት በታሪኩ ገጥሞት አያውቅም። በፋሽስት ጣልያን ወረራ ጊዜ ለጠላት ያደሩ ባንዶች እንኳን ከዛሬዎቹ ብአዴኖች የተሻለ ክብር ነበራቸው። እነሱም ከዛሬዎቹም በተሻለ በጌቶቻቸው ጣሊያኖች ይሰሙ ነበር። በገዢዎቹ ለመወደድ የራሱን ሕዝብ የሚዘልፍ፣ የሚሰድብና የሚያዋርድ እንደ ብአዴን ያለ አዋራጅ ድርጅት በአማራ ምድር አልታየም።

ለዚህም ነው የባህርዳር እና አካባቢው ሕዝብ የብአዴንና የወያኔን አፈናዎችን በጣጥሶ የካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ም. ቁጣውን በባዶ እግሩ አደባባይ በመውጣት የገለፀው። እግር ባዶ መሆኑ ጭንቅላት ባዶ የመሆኑ ያህል የሚያሳፍር አይደለም። ድህነት ወንጀል አይደለም። ነፃ አዕምሮና የሕዝብ ይሁንታ ያገኘ አስተዳደር ካለ ድህነትን ማሸነፍ ይቻላል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ፈታኝ ሁኔታዎችን ተቋቁመው የየካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ምን ሕዝባዊ ተቃውሞ ላደራጁና በተቃውሞውም ለተካፈሉ ሁሉ ያለውን አክብሮት ይገልፃል። ሕዝብ ብሶቱን የሚገልጽበት ሕዝባዊ ተቃውሞ ማደራጀትና መምራት መቻል ትልቅ ነገር ነው። ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ወደ ሕዝባዊ እምቢተኝነት የማደግ እድል አላቸው። ስለሆነም ግንቦት 7 ለባህርዳሩ ሕዝባዊ ተቃውሞ አደራጆችና ተሳታፊዎች "እንኳን ደስ ያላችሁ" በማለት የትግል አጋርነቱን መግለጽ ይሻል።

ግንቦት 7፤ ብአዴንን ከአባላቱ ለይቶ ማየት ይሻል። ከዚህም በተጨማሪ የብአዴንን ከፍተኛ አመራር ከሌላው ለይቶ ይመለከታል። ብአዴን ነፍሳቸውን ሳይቀር ለወያኔ በሸጡ ሰዎች የሚመራ፤ ነፃ የመውጣት ተስፋ የሌለው ራሱ ባርያ የሆነ ድርጅት ነው። አባላቱ ግን ከዚህ የተለዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግንቦት 7 ያውቃል።

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህም በፊትም ደጋግሞ እንደገለጸው፤ በተለያዩ ጊዜያት ራሳቸውን ከወያኔ ባርነት ነፃ ለማውጣት በወሰዱት እርምጃ መስዋእትነት የከፈሉ የብአዴን አባላት መኖራቸውን ያውቃል። ግንቦት 7 ለእነዚህ ቆራጦች ትልቅ አክብሮት አለው። ዛሬም ህሊናቸውን ሙሉ በሙሉ ያልሸጡ የብአዴን አባላት አሉ ብሎ ያምናል። እነዚህ ወገኖቻችን ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የግል፣ የወገንና የአገር ግዴታ አለባቸው ብሎ ያምናል።

ስለሆነም ዛሬም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመን ጥሪዓችንን እናድሳለን።

የብአዴን አባላት ሆይ!!! የገዛ ራሳችሁን፣ የአማራን ሕዝብ እና ኢትዮጵያን እያዋረደ ካለው ብአዴን ተላቀቁ፤ አሊያም እውስጡ ሆናችሁ ድርጅቱን ግደሉት። የብአዴን መኖር ለወያኔ ካልሆነ በስተቀር ለማንም አይበጅም። ነፃነት ካለ ድህነትን በሥራ ማሸነፍ ይቻላል። ሰው ባርያ ሆኖ በሀብት ቢንበሸበሽ ምን ይፈይድለታል?

የብአዴን አባላት ሆይ!!! ወደ ህሊናችሁ ተመለሱ። ራሳችሁንም የበደላችሁትን ሕዝብ የመካስ እድል አድል አላችሁ ተጠቀሙበት። ይህንን ባታደርጉ ግን ለገዛ ራሳችሁ ፀፀት፤ ለልጆቻችሁ ሀፍረትን የምታወርሱ መሆኑን አትዘንጉ። ወያኔ መሸነፉ በጭራሽ የማይቀር መሆኑን እያወቃቸው በድህረ ጣልያን ወረራ ባንዶች ያገኙትን ምህረት እናገኛለን ብላችሁ አታስቡ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሆድ አደሩ አለምነው መኮንን ጉዳይ የተቃውሞ ሰልፉን ለማድረግ እንደ መነሻ ሆነ እንጅ ዋናው ጥያቄ የዲሞክራሲ፣ የነጻነት እና የኢኮኖሚ መሆኑን በርካቶች በመግለጽ ላይ ሲሆኑ፡ የህዝቡን እምቢተኝነት የተመለከቱ አንድ ታዛቢ ለሬዲዮ ክፍላችን እንዳደረሰን ፋሽስቱ ወያኔ እንደተናካሽ ውሻ በድንጋጤ ያገኘውን ሁሉ ለመንከስ ቢሞክርም፣ የተጀመረው ትግል ግን ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ሁዋላ የሚቀለበስ አይሆንም በመለት አስተያየታቸውን አድርሰውናል። ከሰሞኑ በዩክሬን የተመለከትነው የህዝብ እምቢተኝነት ቀጣይ መዳረሻው ኢትዮጵያ ስለመሆኗ አመላካች ነው ሲሉም የባህር ዳርን ህዝብ እምቢተኝነት አወድሰዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለአለፉት 23 አመታት በህወሃት እየተሰደበና እየተረገጠ ተገዝቷል። ጭቁን ህዝቦች በመላው ኢትዮጵያ በቃ ብለው መነሳትና ነጻነታቸውን ማወጅ ይኖርባቸዋል፡ የባህር ዳሩ ሰልፍ ታላቅ ትምህርትን ሰጥቶ አልፏል። ዛሬ ኢትዮጵያዊ አማራ ሲሰደብ ዝም ካልን ነገ ኢትዮጵያዊ ኦሮሞ፡ ኢትዮጵያዊ ትግሬ፡ ኢትየጵያዊ ጉራጌ፡ ኢትዮጵያዊ አፋር፡ ኢትዮጵያዊ ሱማሌ መሰደባቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህ ትግሉ የሁላችንም መሆን ይገባዋል፡፡ እንደ ዩክሬይን ህዝብ አንባገነኖችን ለማስፈርጠጥ በጋራ ቆርጠን መነሳት ያለብን ሰአት አሁን ነው።

## ብአዴን የባህርዳሩ ሠልፍ እንዳይሳካ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

"ቢቀዳ ቢጨለጥ አንድ የርእዮት አለም ሰው የነበረው መለስ ዜናዊ ነው" የሚሉት አቶ አለምነው፣ ሌላው ሁሉ ተከታይ" ነው በማለት የኢህአዴግን አባላት ሳይቀር ከላይ እስከታች ተከታዮች አድርገው ፈርጀዋቸዋል። " ሱፍ ለብሶ በመሄድ" አይደለም ሲሉም በአገሪቱ ባሉ ምሁራንና በኢህአዴግ መሪዎች ላይ ሳይቀር ተሳልቀውባቸዋል።

ኢህአዴግ ከአቶ መለስ ሞት በሁዋላ አዳዲስ ሃሳቦች የሚያመነጭ የርእዮት አለም ሰው ሰው የለውም ማለት ነው ሲሉ በስብሰባው ላይ የተሳተፉ አንዳንድ የብአዴን አባላት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ከ 6 ሚሊዮን የኢህአዴግ አባላት መካከል እንዴት አንድ ሰው እንኳ አዲስ ሃሳብ የማመንጨት ብቃት የሌለው ይጥፋ በማለት አባላቱ ጠይቀዋል።አቶ አለምነው አማራውን በተመለከተ የተናገሩት አቶ መለስ በተደጋገሚ ሲጽፉትና ሲናገሩት የነበረውን ያሉት አንዳንድ አመራሮች፣ ብአዴን በአማራው ስም የተደራጀ የህወሃት ጉዳይ አስፈጻሚ ድርጅት ነው እየተባለ የሚነገረው እውነት በመሆኑ፣ ድርጅቱን ከህወሃት ፈልቅቆ ለማውጣት የውስጥ ትግል እየተካሄደ መሆኑንም አክለዋል።

## የፓይለት ሃይለመድህን አበራ እናት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወያኔን በአለም ህዝብ ፊት ዳግም የሸንፈት ፅዋ ማስጎንጨት አለብን በማለት አስተያየታቸውን አድርሰውናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በስዊዘርላንድ በርን ከተማ ዉስጥ የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሃይለመድህን አበራ አፋጣኝ ፍትህ እንዲያገኝ ጠይቀዋል። ሠልፈኞቹ "ሃይለመድህን ወንጀለኛ አይደለም፣ ወንጀለኛው የኢትዮጵያ መንግስት ነው፣ አሸባሪው ወያኔ ነው፣ ህዝቡን አግቶ የያዘው የኢትዮጵያው አሸባሪ መንግስት ነው፣ ዲሞክራሲና ፍትህ ለኢትዮጵያ" የሚለዩና ሌሎችም መፈክሮች ተስተጋብተዋል።በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ባዘጋጀው በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል። ከስዊዘርላንድ ሌላ ኖርዌይ ኦስሎ ዉስጥ በሚገኘዉ በስዊዘርላንድ ኢምባሲ ፊት ለፊት ላይም ሌላ ሰልፍ ረዳት አብራሪ ሃይለመድህንን በተመለከተ የተካሄደ ሲሆን ሰልፈኛዉ የሃይለመድህን አበራ የጥገኝነት ጥያቄ አፋጣኝ እልባት እንዲያገኝ ጠይቋል።

## የኦሮምያ ክልል አለማየሁ አቶምሳን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መንግስቱ ጋር ተግባብቶ የሚሰራ እንዲሆን እንደሚፈለግ እኘሁ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰዎች ይናገራሉ። በአባ ዱላ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሰዎች ከሙስና ጋር በተያያዘ ድርጅቱን አደጋ ውስጥ በመጣላቸው በፌደራሉ መንግስት በዙም አይደገፉም። ከሁለቱም ቡድኖች ወጣ ያለ አዲስ ሰው ለማገኘት ኦህዴድ ፈተና እንደሆነበትና ምናልባትም ሽኩቻው በዚህ ከቀጠለ የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት ስልጣኑን ተረክበው ሊቀጥሉ ይችላሉ የሚለውን ግምት እያጠናከረው መምጣቱን ይገልጻሉ።

---

# ጥፋተኛ ጥፋቱን በይቅርታ እንጂ በዉሸትና በዕብሪት መሸፈን አይችልም

በቅርቡ አንድም የወያኔ ጌቶቹን ለማስደሰት ደግሞም ከህወሃት ካድሬዎች ስድብና ግልምጫ የማያድን ጎደሎ ስልጣን ለማግኘት ሲል ተወልዶ ያደገበትንና እመራዋለሁ የሚለዉን የአማራን ህዝብ ክብርና ታሪክ ያጎደፈዉና ያዋረደዉ የአለምነዉ መኮንን አስጸያፊ ንግግር በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያንን ያስቆጣና ያነሳሳ ጉዳይ ሆኖ መሰንበቱ ይታወሳል። ይህ የአማራን ህዝብ ማንነትና ይህ ጀግና ህዝብ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ያለዉን አኩሪ ቦታ ያላገናዘበና ባልተሞረደ አንደበት የተነገረ አስጸያፊ ንግግር ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተዉን የአማራን ህዝብ ብቻ ሳይሆን አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚኖሩትን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን አስቆጥቷል። አይናቸዉ ከገንዘብና ከሥልጣን ዉጭ ሌላ ምንም ነገር የማይመለከት ለሆዳቸዉ ብቻ ያደሩ ሰዎች የተከፈተ ሆዳቸዉንና ማለቂያ የሌለዉ የሥልጣን ጥማታቸዉን ለማርካት ሲሉ ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይሉ ወያኔ በሥልጣን ላይ የቆየባቸዉ ያለፉት ሃያ ሦስት አመታት በግልጽ አሳይተዉናል። ሆኖም ግን አይናቸዉ የታወረና ጭንቅላታቸዉ ባዶ የሆነ ሰዎች በነገሱበት በወያኔ ስርዐት ዉስጥም ቢሆን የሚጠሉትን፤ የሚንቁትንና የገዛ ወገኖቹን የገቡበት ቦታ ሁሉ እየተከተሉ ወደ አገራችሁ ግቡ እያሉ የሚያፈናቅሉ ዘረኞችን ለማስደስት ሲል ስቃይ የበዛበትን የራሱን ህዝብ ያዋረደ ከሀዲና ሂሊና ቢስ ሰዉ ያየነዉ አንድ አለምነዉ መኮንንን ብቻ ነዉ። አለምነዉ የተናገራቸዉን አጥንት የሚሰብሩ የንቀት ቃላት ይሀንን ከንቱ ሰዉ ባወገዝን ቁጥር እየደጋገምን ብንጠቅስ በአንድ በኩል የወያኔን ዘረኞች አላማ ያራምዳል ብለን ስለምናምን በሌላ በኩል ደግሞ እንደዚህ አይነቱን ጸያፍ ንግግር መደጋገም ሂሊናችን ስለማይፈቅድንና የጠፈፈ ቁስል መቆስቆስ ይሆናል ብለን ስለምንሰጋም ንግግሩን አንደግመዉም።

አሜሪካንን በመሳሰሉና በዕድገት ወደፊት በገፉ አገሮች ዉስጥ ዉሻ የሚታወቀዉ የሰዉ ልጅ ታማኝ ወዳጅ በመባል ነዉ። ዉሻ ባለቤቱን ለማስደስት ጭራዉን ከመቁላት ባሻገር የባለቤቱን እግር ይልሳል፣ ይንበረከካል፣ እግር ስር ይተኛል፣ ደግሞም አምጣ ብለዉ የወረወሩለትን ነገር እየሮጠ ሄዶ ያመጣል። የሚገርመዉ እንስሳዉ ዉሻ እንኳን እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያደርገዉ ለባለቤቱና ለለመደዉ ወዳጁ እንጂ ለሌላ ለማንም ሰዉ አያደርግም። ዉሻ ባለቤቱንና ወዳጁን በተለይ ደግሞ የሱንና የባለቤቱን ጠላቶች ለይቶ ያዉቃል፣ ስለዚህም ዉሻን ባለቤትህን ንከስ ብለን ያንን የሚወደዉን ስጋ ያሻንን ያክል ብናሸከመዉ እኛዉ ላይ መልሶ ይጮህብን እንደሆነ ነዉ እንጂ ዉሻ ባለቤቱን በፍጹም አይነክሰም።

ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ እነ አለምነዉን የመሳሰሉ ለወያኔ ያደሩ ሂሊና ቢሶች፣ ሹምባሾች፣ ምስለኔዎችና ሆዳሞች አንድ የጎደላቸዉ ትልቅ ነገር ቢኖር የዉሻን ያክል ታማኝ መሆን ነዉ። እነ አለምነዉ እናስተዳድረዋልን ለሚሉት ህዝብ ታማኝነት ቢኖራቸዉ ኖሮ ዛሬ እነሱ እራሳቸዉ፣ የሚመሩት የአማራ ህዝብም ሆነ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአገሩ ተስድዶ እንደ አዙሪት በየአገሩ ከሚዞር በገዛ አገሩ ተከብሮ በወግና በማዕረግ ይኖር ነበር።ችግሩ "ባለቤቱ ያቀለለዉን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለዉም" ነዉና የኢትዮጵያ ህዝብ በእነ አለምነዉና መሰሎቹ የተነሳ ኢትዮጵያ ዉስጥም ከኢትዮጵያ ዉጭም መብቱንና ነጻነቱን ተገፍፎ የሚኖር ባተሌ ህዝብ ሆኗል። የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት ነኝ ባዩ አለምነዉ መኮንን እንደማናችንም እግዚአብሄር በአምሳያዉ የፈጠረዉ ሰዉ ነዉ፣ ታድያ ለምንድነዉ ሂሊና የሌላቸዉና ነገሮችን አመዛዝነዉ የመመልከት ባህሪይ የልታደላቸዉ እንስሳት እንኳን የማያደርጉትን አስጸያፊ ነገር እሱ በገዘ ወገኖቹ ላይ ያደረገዉ? በእርግጥ ይህንን ጥያቄ አለምነዉ በጥቅም የተገዛ ወይም ለሆዱ ያደረ ሰዉ ነዉ ብለን በቀላሉ መልሰን ማለፍ እንችል ይሆናል፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ከብዙ አፍሪካዉያን በተለየ መልኩ ነጻነቱንና አንድነቱን ጠብቆ መኖር የቻለበትን ምክንያት ለምንረዳ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠዉ መልስ የችግሩን ያክል የተወሳሰበ መሆኑን እንረዳለን። ይህንን ስለምንረዳም ነዉ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከወያኔ መዳፍ ዉስጥ ፈልቅቆ ለማዉጣት መከፈል ያለበት መስዋዕትነት የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ቤት ያንኳኳል የምንለዉ።

ወያኔ ወይም ህወሀት በሚባለዉ የዘረኞች ድርጅት ዉስጥ የታቀፉ ሰዎች ስልታዊ አላማ አንድና አንድ ብቻ ነዉ- እሱም ኢትዮጵያ የምትባል ገንዘብና ንብረት የምትታለብ ላም ወተቷ እስኪነጥፍ ድረስ ብቻችንን እንለባት የሚል የስስት አላማ ነዉ። ይህንን የስስት አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የነደፉት እስትራቴጂ ደግሞ የአላማችን ዋነኛ ጠላት ነዉ ብለዉ የሚያምኑትን የአማራዉን ህዝብ መግደል፣ ማሰር፣ ማሳደድ፣ ማፋናቀል፣ መደብደብና ማዋረድ ነዉ። ይህንን ከጠላቶቻችን ከነሙሶሊኒና ግራዚያኒ የተማሩትን አማራዉን የማሳነስና የማጥፋት ስልት ደግሞ እግራቸዉ አዲስ አበባን ከረገጠበት ቀን ጀምሮ የአማራዉን ግዛት ቆርሰዉ የራሳቸዉ በማድረግና አማራዉን በመግደል፣ በማሳደድና በማሰር በተግበር አሳይተዉናል ዛሬም እያሳዩን ነዉ።

የወያኔ ዘረኞች የቂም በቀል እርምጃዎች ሁሉ ያነጣጠሩት በአለምነዉ መኮንንና በወገኑ የአማራ ህዝብ ላይ ነዉ፣ ወያኔ ወልቃይት ጠገዴን ቆርሶ የወሰደዉ ከአለምነዉ መኮንንና ከወገኑ ከአማራ ህዝብ ላይ ነዉ፣ ከጉራ ፈርዳና ከቤንሻንጉል አካባቢዎች ሂድ ከዚህ ተብሎ የተፈናቀለዉ ህዝብ አለምነዉ መኮንን እመራዋለሁ የሚለዉ የአማራዉ ህዝብ ነዉ። ታድያ አለምነዉ መኮንን እሱንና የገዛ ወገኖቹን ለዘህ ሁሉ ዉርደትና መከራ የዳረጉትን የወያኔ ዘረኞች ለማስደስት ሲል የተወለደበትን ማህበረሰብ መሳደቡ ምን ይባላል? ወያኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስተማረዉ መጥፎ ነገር ቢኖር ዘረኝነት ነዉ፣ አለምነዉ መኮንን በዚህ መጥፎ የወያኔ ትምህርት ተለክፈ ብለን ብናምን እንኳን ዘረኝነት የራስን ዘር ከሁሉም በላይ እንድናይና ሌሎችን እንድንጠላና እንድንንቅ ያደርገናል እንጂ የራሳችንን ዘር እንድንሰድብና እንድናዋርድ አያደርገንም። ታድያ አለምነዉ መኮንንን የተጠናወተዉ የወያኔ ዘረኝነት ነዉ ወይስ የሚያድኑትን እያስጠላ የሚገድሉትን የሚያስወደድ የታምራት ላይኔ በሽታ ነዉ?

ሌላዉ የአለምነዉ መኮንንና የብአዴን ችግር አለምነዉ ያንን አሳፋሪ ንግግር ካደረገና ንግግሩ የህዝብ ጆሮ ዉስጥ ገብቶ አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ብዙ ሰዎችን ካስቆጣ በኋላ ጥፋታቸዉን ተረድተዉ ህዝብን ይቅርታ አለመጠያቃቸዉና ሌላ ቢቀር አስተዳድረዋለሁ የሚለዉን ህዝብ ሙልጭ አድርጎ የሰደበዉን ሰዉ ህዝብን ከመምራት ሀላፊነት ቦታ ላይ እንዲነሳ አለማድረጋቸዉ ነዉ። አለምነዉ መኮንን የአማራን ህዝብ ከተሳደበ በኋላ ወያኔም ሆነ ብአዴን ከመጋረጃ ጀርባ የተባባሉትን ነገር ባናዉቅም ስድቡን አስመልክቶ በግልጽ ህዝብ እንዲያዉቀዉ የወሰዱት ምንም እርምጃ እንደሌለ ግን በሚገባ እናዉቃለን። ይህ የሚያሳየን ወያኔና ብአዴን ለህዝብና ለአገር ምንም ደንታ እንደሌላቸዉ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ሁለት ጸረ ህዝብ ድርጅቶች ህዝብን እንዳሻን ረግጥን መግዛት እንችላለን የሚሉ ዕብሪተኞች እንደሆኑ ነዉ። የወያኔ ሹሞችና በየቦታዉ የበተኗቸዉ ሆዳም አፈቀላጤዎቻቸዉ የአለምነዉ መኮንንን መረን የለቀቀ ንግግር ለማስተባበልና እንዲያዉም ተባለ የተባለዉ ንግግር ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሆን ብለዉ ያቀነባበሩት የፈጠራ ስራ ነዉ እያሉ ህዝብን ለማሳመን ብዙ ደክመዉ ነበር፣ ነገርግን ብዙም ሳይቆይ ግለሰቡ በባዕዴን ስብሰባ ላይ የደረገዉ ንግግር በመጀመሪያ በኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን ከዚያም በማህበራዊ ሜድያዎችና በተለያዩ ድረገጾች ላይ በብዛት መሰራጨት ሲጀምር ወያኔና ቡችሎቹ ማስተባበሉን ትተዉ ሳይወዱ በግድ ዝምታን መርጠዋል።

ወያኔና ብአዴን ህዝብን ሰድበዉና አዋርደዉ ዝምታን ቢመርጡም የተሰደበዉ የኢትዮጵያ ህዝብና መሪ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ግን የአማራን ህዝብ አስጸያፊ ስድብ የሰደበዉ አለምነዉ መኮንን ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ እስካልተወሰደበት ድረስ ዝም እንደማይሉ ለሚመሩት ህዝብም ለወያኔም ይፋ አደረጉ። በተለይ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲና መላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አለምነዉ መኮንን የሰደበዉ የአማራ ህዝብ በክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር ዉስጥ በነቂስ ወጥቶ ተቃዉሞዉን እንዲያሰማ የሰላማዊ ሠልፍ ጥሪ አደረጉ። ይህ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሠላማዊ ሠልፍ ጥሪ ለህዝብ ከተላለፈና ህዝቡ ቁጣዉን ከመግለጽ ወደኋላ እንደማይል ከተረዱ በኋላ ነበር እነ አለምነዉ መኮንን ሰድብዉት እንዳሻህ ብለዉ የዘጉትን ህዘብ በፕሬስ መግለጫ ስም እንደገና ማደናገር የጀመሩት። እዚህ ላይ አንድ እጅግ በጣም የሚያናድድና አንጀት የሚያሳርር ነገር ቢኖር ባለፈዉ ሐሙስ አለምነዉ መኮንን በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በጉጉት ይጠበቅ የነበረዉ ይህ ግለሰብ የሰደበዉን ህዝብ ይቅርታ ይጠይቃል ተብሎ ነበር። ሆኖም አለምነዉ መኮንን፣ብአዴንና ህወሀት ከዕባብ እንቁላል እርግብ እንደማይጠበቅ በግልጽ አሳይተዉናል።

ባለፈዉ ኃሙስ ዬካቲት 13 ቀን 2006 ዓም አለምነዉ መኮንን የአገር ዉስጥ ጋዜጠኞች ያንን መረን የለቀቀ ስድቡን አስመልክተዉ የጠየቁትን ጥያቄ ሲመልስ እዉነትም "ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር ይሻላል" የሚያሰኝ የቂል መልስ ስጥቷል። ነፃ ሜድያ በሌለባት ኢትዮጵያ ዉስጥ እንዳሰኘዉ መለፍለፍ የለመደዉ አለምነዉ መኮንን "ተቃዋሚዎች አለ ያሉትን ነገር እኔ በፍጹም አላልኩም . . . እኔ ለህዝብ ክብር ያለኝ ሰዉ ነኝ በማለት ነገሩ እየቆየ ሲሄድ እሱ እራሱ የተናገረዉ ንግግር ገርሞት "እኔ እንዴት እንደዚህ ልል እችላለሁ"ሲል ጋዜጠኞች የጠየቁትን ጥያቄ መልሶ እራሱን ጠይቋል። ይህ እፍረተ ቢስ ሰዉ ህዝብን የተሳደበዉ አልበቃ ብሎት ጭራሽ ጥፋቱን በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ለማላከክ ሲሞክር ተድምጧል። ማንም ሰዉ ተናገር ብሎ ሳያስገድደዉና ቁጭ ብለዉ የሚያዳምጡት ሰዎች እየሳቁ በራሱ አንደበት የተናገረዉን ፀያፍ ንግግር ተቃዋሚዎች መሪዎችን ከህዝብ ለመነጠል ሆን ብለዉ የሰሩትና በቆርጦ ቀጥል የኮምፒተር ዘዴ ያቀነባበሩት ነገር ነዉ እንጂ ዬኔ ንግግር አይደለም ሲል የራሱን ድምፅ ዬኔ አይደለም ሲል ሽምጥጥ አድርጎ ክዷል።

ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ተምራ የምትመጣዉን ነገር እናዉቃለንና ከወያኔ ዘረኞች ጋር ለአመታት የከረመዉ አለምነዉ መኮንን በመዋሸቱ ብዙም ላንፈርድበት እንችላለን፣ ደግሞም ወያኔና ዉሸት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸዉና ወያኔን ባየን ቁጥር ትዝ የሚለን እንደ ሰዉ ቆሞ የሚሄደዉ ዉሸቱ ነዉና የአለምነዉ ዉሸት በፍጹም አይገርመንም። ይልቅ እኛን የገረመን አለምነዉ መኮንን የራሱን ድምጽ ዬኔ አይደለም ማለቱ ነዉ። መቼም አንድ ሰዉ ለይቶለት አማኑኤል ካልገባ በቀር እኔ "እኔ" አይደለሁም ብሎ የመናገር ደረጃ ላይ የሚደርስ አይመስለንም። ደግሞስ አለምነዉ መኮንን የማንሰማዉ መስሎት ባልተገራ አንደበቱ ህዝብን ሲሳደብ በድንገት ሰምተነዉ ነዉ እንጂ እስኪ እግዚአብሄር ያሳያችሁ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የባህርዳር ሠልፈኛ ያነሳዉ ጥያቄ የሁሉም ኢትዮጵያዉ የለዉጥ ፍላጎት ጥያቄ ነዉ

ያለፈዉ እሁድ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶልስ እምነት ተከታዮች ልዩ ቀን ነበርች። ለወትሮዉ ክረስቲያኑ በዚህች ቀን የሁለት ወሩን የኩዳዴ ጠዮም ለመቀበል ከቤተሰቦቹ ጋር በዝግጅት ነበር የሚያሳልፈዉ። በዚህ አመት ግን ይህንን ባህሉንና ወጉን ትቶ ከፍ ዝቅ አድርገዉ የሰደቡትን መሪዎቹን ለመቃወም በባዶ እግሩ ሰላማዊ ሠልፍ በማድረግ አሳልፏል። በዚሁ “ቅበላ” በመባል በሚታወቀዉ ቀን የባህርዳርና የአካባቢዋ ነዋሪዎች አንድነትና መኢአድ በጋራ በጠሩት ሰልፍ ላይ በነቂስ ወጥተዋል። “ህዝብን እያዋረዱ መግዛት አይቻልም፣ብአዴን ኢህአዴግ የአማራን ህዝብ የመግዛት የሞራል ልእልና የለውም፣ ህዝብ ከእርስት ማፈናቀል ይቁም፣ ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር ይሻላል፣ ነጻነት የሌላት አገር ጨለማ ናት፣ ገበሬው በገዛ መሬቱ ስደተኛ አይሆንም” የሚሉና ሌሎችም መፈክሮች ተስምተዋል።

“ዛሬ ታላቅ ደስታ ተስምቶኛል፣ የአመታት ህመሜ ተፈውሷል” ሲል የተናገረው የቀበሌ 7ቱ ነዋሪ ማሙሽ፣ ሰልፍ እንደሚደረግ ከሰማበት ጊዜ ጀምሮ ሲቀሰቅስ መቆየቱን ተናግሯል። ሌላዉ እዚያዉ ባህር ዳር አካባቢ መሸንቲ ዉስጥ ነዋሪ የሆነዉ ሙላት የተባለ ሰልፈኛ ድግሞ፤ በተቃውሞ ሰልፉ ላይ የተገኘሁት በአገዛዙ ተማርሬ ነው ይላል። ለምን ተማረርክ በማለት ዘጋቢያችን ላቀረበችለት ጥያቄ፣ “ምን የማያስመርር ነገር አለ፣ ሁሉም ነገር እየተበላሸ እንጅ እየተሻሻለ ሲሄድ አታይም፣ ይህም አልበቃ ብሎ ይዘልፉናል” በማለት በሰልፉ ላይ የተገኘበትን ምክንያት ገልጿል።

አቶ አለምነው መኮንን የአማራን ህዝብ መዝለፋቸውን ተከትሎ የተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የባህርዳር ነዋሪዎች በኢትዮጵያ ባንዲራ፣ አንዳንዶችም ጥንታዊት ኢትዮጵያን በሚወክሉ የጀግንነት ማጌጫዎች ተውበው በአደባባይ ተይተዋል።ይሄ ህዝብ ማስፈራሪያዎችን ሁሉ ጥሶ፣ የቀን አበል ሳይሰጠው ለነጻነቱ በፍላጎቱ የወጣ ህዝብ ነው ያለው መኮንን፣ ገዢው ፓርቲ ይህንን ሰልፍ ለማውገዝ ሌላ ሰልፍ ሊያዘጋጅ እንደሚችል ይናገራል።“ወጣቱ ፣ ሽማግሌው ሴቱ ወንዱ ተነስቷል” የሚለው ሌላው ነዋሪ፣ ህዝቡ ለነጻነቱ ሲጠይቅ መዋሉን ገልጿል።“ከሰለፉ ማግስት ባህርዳር እንዴት ናት?’ በማለት ሲጠየቅም፣ ” ህዝቡ ደስ ብሎት በእየቤቱ እየተወያየ ነው” ብሎአል ። ሌላው አስተያየት ሰጪ ደግሞ በሰልፉ ላይ የታየውን ዲሲፒሊን አድንቋል።የአቶ አለምነው መኮንን ጉዳይ የተቃውሞ ሰልፉን ለማድረግ እንደ መነሻ ሆነ እንጅ ዋናው ጥያቄ የዲሞክራሲ፣ የነጻነት እና የኢኮኖሚ መሆኑን ገልጿል። ”ኢህአዴግ እንደተናካሸ ውሻ በድንጋጤ ያገኘውን ሁሉ ለመንከስ ቢሞክርም፣ ትግሉ ግን ወደ ሁዋላ የሚቀለበስ አይመስለኝም ሲል አስተያየቱን አክሏል።

## ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ በአባይ ግድብ ግንባታ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ሪፖርተር ዘገበ

የሙስናዋ እመቤት እየተባለች የምትታወቀዉ የአዜብ መስፍን የእህት ልጅ በሆነች ግለሰብ ስም የተመዘገበዉ ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ የተባለዉ ኩባኒያ በህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለዉ አፍቃሬ ወያኔ የሆነዉና አገር ዉስጥ የሚታተመዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ።ሪፖርተር ጋየጣ ባለፈዉ እሁድ እትሙ እንደገለጸው ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ” በህዳሴው ግድብ ላይ 60 ከመቶውን የትራንስፖርት፣ ሎጂስቲክና አፈር የማንሳት ሥራዎችን ከሳሊኒ በተቋራጭነት በመውሰድ እየሠራ እንደሚገኝም ባለፈው አመት ኩባንያው በቀድሞው ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን የእህት ልጅ በወ/ሮ አቲኮ ስዩም አምባየ መመስረቱን ፣ በግልገል ጊቤ አንድ እና ግልገል ጊቢ ሁለት የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክቶች ስሚንቶ እና የግንባታ እቃዎችን እንዲሁም ከፍተኛ ማሺነሪዎችን በማቅረብ መሳተፉን ዘግቦ ነበር። ይህ ኩባንያ በአባይ ግድብ ግንባታ ዙሪያ ከሳሊኒ በመቀጠል ከፍተኛውን ድርሻ መያዙን በወቅቱ ኢሳት ዘግቧል።“ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ፣ በደረጃ አንድ ተቋራጭነቱ በአየር ማረፊያ፣ በመንገዶች፣ በሕንፃ ግንባታ፣ በነዳጅ ቁፋሮ ሥራዎችና በሌሎችም መስኮች መሰማራቱን የገለጸው ሪፖርተር፣ በእህት ኩባንያዎቹ በኩል በአበባ እርሻ፣ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መስኮች ሲሠራ የቆየ አገር በቀል ኩባንያ ነው፡፡ ” ብሎአል ሪፖርተር።

ወ/ሮ አቲኮ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ከአንድ አነስተኛ የኪራይ መኪና ውጭ ይህ ነው የሚባል ሃብት አልነበራቸውም። ግለሰቡዋ በአጭር ጊዜ ውስጥ የናጠጡ ሀብታም ለመሆን የቻሉት በወ/ሮ አዜብ መስፍን ድጋፍ እንደሆነ ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁ ሰዎች ይናገራሉ፡ጋዜጣው እንደዘገበው ወርኪድ ከጀርመኑ ባወር ኩባንያ ጋር በመነጋገር ከባድ ማሽነሪዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ከአባይ ግድብ እስከ ነዳጅ ፍለጋ ስራዎች ያሉ ቁፋሮዎችን ያካሂዳል።

## አዲስ አበባን በ24 ሰዓት የቴሌቭዥን አገልግሎት ለመሸፈን የተደረገዉ የወያኔ ጥረት ከሸፈ

ኢቲቪን የራሱ ንብረት አድርጎ ላለፉት ሃያ ሁለት አመታት የፕሮፓጋንዳ ቱልቱላዉን ሲረጭ የከረመዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ይህ አልበቃ ብሎት አዲስ አበባ ዉስጥ የጀመረዉ ሰፋ ያለ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስርጭት ፕሮጀክት ስራዉ ከተጀመረ በኋላ መክሸፉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙት የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ይሄዉ ወያኔ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የመገናና ብዙሃን ኤጀንሲ በኩል የጀመረዉና የመረጃ ውጤቶችን ለሕዝብ ያድረሱልኛል በሚል ከፍተኛ ወጪ በአዲስአበባ ማዘጋጃ ቤት ሕንጻ ውስጥ የገነባዉ ዘመናዊ ስቱዲዮ በአቅም ማነስ ምክንያት ማሳካት ሳይችል ቀርቷል፡፡

የኦሮሚያ፣ የአማራ እንዲሁም የሶማሌ ክልሎች በዓረብ ሳተላይት ላይ ጭምር የክልሎቻቸውን ዜናዎችና መረጃዎች በቴሌቪዥን እያሰራጩ ሲሆን የአዲስአበባ አስተዳደርም በተመሳሳይ መንገድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስርጭቱን ከ6፡30 ሰዓት ወደ 24 ሰዓታት ፤ራዲዮ ፕሮግራሙን ስርጭት ከ18 ሰአታት ወደ 24 ሰዓታት ለማሳደግ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጥረት ሲያደረግ መቆየቱን የአስተዳደሩ ምንጮች አስታውሰዋል፡፡ የመሳሪያዎች ግዥና ተከላ፣ የቢሮ ዝግጅት፣ የሰው ሃይል ቅጥር ቢጠናቀቅም በታህሳስ ወር በ2006 ይጀመራል ቢባልም በይፋ ባልተገለጸ ምክንያት ስራው ሳይጀመር ቀርቷል፡፡

የአስተዳደሩ ምንጮች እንደሚናገሩት የቴሌቪዥንና የራዲዮ ስርጭቱን ማሳደግ ያልቻለው ኤጀንሲውን የሚመሩ ሙያው የሌላቸው ካድሬዎች አቅም ማነስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ኤጀንሲው በያዝነው ኣመት ዕቅዱ የ2007 ዓ.ም ሃገር አቀፍ ምርጫን ዴሞክራሲዊ እና የህዝብ ተሳትፎን ለማረጋገት የሚያስችሉ የኮምኒኬሽን ስራዎች በብቃት እንዲተገበሩ ማድረግ፣ በዋና ዋና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በህዝቡና በከተማ አስተዳደሩ መካከል መግባባትና መተማመን የሚፈጥሩ የኮምኒኬሽን ስራዎችን ማከናወን ከያዛቸው ዕቅዶች ግንባር ቀደሞቹ ነበሩ።

በአሁኑ ወቅት በ1991 ኣ.ም የወጣው የብሮድካስት አዋጁ የራዲዮና ቴሌቭዥን ጣቢያ በግል ማቋቋምን የፈቀደ ቢሆንም ኢህአዴግ መራሹ መንግስት “የሕዝቡ ንቃተ ሕሊናው አላደገም” በሚል አዋጁን ካለመተግበሩም በላይ ኢቲቪን የተለያዩ ፕሮግራም አልባ ቻናሎች እንዲከፍት በማድረግ እንዲሁም ክልሎች በዓመት ከሚመደብላቸው አነስተኛ በጀት ቀንሰው ለቴሌቪዥን የሳተላይት ስርጭት የኪራይ ክፍያና የማሰራጫ መሳሪያዎች ግዥና ተከላ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጡ እያበረታታቸው መሆኑና ክልሎችም በፉክክር ውስጥ መግባታቸው ታውቋል።በሌላ ዜና ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ የሚሰሩ የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኞች በግቢው የጸጥታ ዴስክ በኩል ከፍተኛ ፍተሻ እየተደረገባቸው ነው።

በከተማ አስተዳደሩ የሚሰሩ የተለያዩ የዕለት ከዕለት ፖለቲካዊ ተግባራት በመኖራቸውና ከህዝቡ ልማታዊ እንቅስቃሴ ጋር የሚተሳሰሩ ቀጥተኛ መረጃዎች ሲያጋጥሙ በተደጋጋሚ ለኢሳት መረጃ በመድረሱና ህዝቡ እንዲያውቀው መደረጉን ተከትሎ ከተማ አስተዳደሩ ያልወደደው በመሆኑ የመረጃ ልልውጡን ለማስቀረት በሚያመች መልኩ በሚመስል ሁኔታ ከቁልፍ ባለስልጣናት በስተቀር፣ ወደ ግቢ የሚገቡ ሰዎች፣ የውስጥ ሰራተኞችን፣የውጭ የከተማ አስተዳድሩ ሰራተኞችን፣ ለተለያየ ጉዳይ የሚመጡ ባለጉዳዮችና ሌሎችም ሰዎች ጭምር ወደ ግቢው ሲመጡ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ መታወቂያቸው በጥንቃቄ ታይቶ መኪኖቻቸው ጭምር በሚገባ ተፈትሾ እንዲገቡ እየተደረገ ነው።

የተለያዩ መረጃዎች እየወጡብን ነው የሚለውን ስጋት ለማስቀረት ተብሎ በር ላይ በፈረቃ በሚቆሙ የጥበቃ ፖሊሶች የሚሰሩ ሲሆን የፍተሻውን ምክንያት ተከትሎ በተለይ የውስጥ ሰራተኞቻቸው ጧት ለስራ ሲገቡ ብዙ ሰዓት ስለሚቆሙ በከፍተኛ ምሬት ውስጥ ናቸው፡፡ከዚህ በፊት በግቢው ውስጥ ከሚገኘው የሰራተኞች መመገቢያ አዳራሽ ብዙ ሰራተኞች ወደ ግቢው መጥተው ምሳ ላይ ለመጠቀም ይፈቅድላቸው የነበሩት የከተማ አስተዳድሩ የውጭ ሰራተኞች የፍተሻውን ስራ ጫና ለመቀነስ ሲባል እንዳይገቡ ተደርጓል፡፡የጥበቃ ፖሊሶች የውስጥና የውጭ ሰራተኞችን መለየት ባለመቻላቸው ና ማንም ሳይፈተሽ መግባት እንደማይችል ስለተነገራቸው የመስተዳድሩ ሰራተኞች ጧት ከቤታቸው ሲወጡ መርሳት ከሌለባቸው ዋነኛ ነገር መታወቂያ ሆኗል፡፡

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ጥፋተኛ ጥፋቱን በይቅርታ እንጂ በዉሸትና

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አለምነዉ መኮንንን ማን ከቁም ነገር ቆጥሮት ነዉ የሱን ተራ ንግግር አየቆረጠ የሚቀጥለዉ? ማንስ ስራ የፈታ ሰዉ ነዉ የራሱንና የኮምፒተሩን ግዜ የአለምነዉ መኮንንን ቆሻሻ ንግግር ቆርጦ በመቀጠል የሚያጠፋ?
ሌላዉ የአለምነዉ መኮንን ጉድ ይህ ሴራ ተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን ከህዝብ ለመነጠል የሚያደርጉት ሴራ ነዉ ብሎ መናገሩ ነዉ። ወይ ጉድ . . . " ወግ ነዉ ሲዳሩ ማልቀስ" ይላል የአገራችን ሰዉ። ለመሆኑ ጭንቅላተ ባዶዎቹ የወያኔና የብአዴን መሪዎች ቀድሞዉኑ ከህዝብ ጋር መቼ ገጥመዉ ያዉቃሉና ነዉ ተቃዋሚ ድርጅቶች እነሱንና ህዝብን ለመነጣጠል እያሴሩ ነዉ ተብሎ የሚነገረዉ? ወንድምዬ የምትሰማኝ ከሆነ እናንተና ህዝብ ዉኃና ዘይት ናችሁ፤ ተገናኝታችሁም አንድ ላይ ሆናችሁም አታዉቁም። በዚህ ስድባችሁ፤ ክህደታችሁና ዕብሪታችሁ ደግሞ ለወደፊትም ቢሆን ከህዝብ ጋር አትገጥሙም። ከህዝብ የነጠላችሁ ክፉ ስራችሁና መጥፎ ጠባያችሁ ነዉ እንጂ ተቃዋሚዎች አይደሉም።

አለምነዉ መኮንን እሱ እራሱ የአማራ ተወላጅ ነዉ፤ ያንን የመሰለ አስጸያፊ ንግግር የተናገረዉም በአማራ ህዝብ ላይ ነዉ፤ሆኖም በዘለፋዉና በዉርደቱ አንጀቱ ያረረዉ ወይም ዘለፋዉ ያነጣጠረዉ በአማራ ህዝብ ላይ ብቻ ነዉ ብለን የምናስብ ሰዎች ካለን እኛም ዘለፋዉን እንደሰነዘረዉ ሰዉ እራሳችንን ስተናል፤ ወይም ዋነኛዉ የወያኔ ወጥመድ ዉስጥ ገብተናል አለዚያም አርቆ የመመልከት ችሎታችን ከከዳን ቆይቷል ማለት ነዉ። ዘለፋዉና ንቀቱ የተሰነዘረዉ በሁላችን ላይ፤ ነዉ፤ የተዋረድነዉም ሁላችንም ነን፤ ስለሆነም አለምነዉንና አቅፈዉት ከለላ የሰጡትን ሁሉ ለፍርድ ለማቅረብ የሚደረገዉ ትግል የሁላችንም ትግል መሆን አለበት። ባህር ዳር ዉስጥ የታየዉ ህዝባዊ ቁጣ በመላዉ ኢትዮጵያ እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጥሎ ወያኔ የገነባዉን ዘረኛ ስርዐት ለብልቦ ከምድረ ኢትዮጵያ እስኪያጠፋ ድረስ ትግላችን መቀጠል አለበት። በዚህ ትግል ዉስጥ "እኔ" ወይም "አንተ" የሚባል ቃል በፍጹም ሊኖር አይገባም። የትግላችን ብቸኛ መነሻና መድረሻ "እኛ " ብቻ መሆን አለበት። ወያኔን አጥፍተን እንደ ህዝብና እንደ አገር በሠላም፤ በነፃነትና በብልጽግና መኖር የምንችለዉ ኢትዮጵያዊነታችን "እኛ" በሚለዉ አስተሳሰብ ላይ ሲገነባ ብቻ ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የወያኔን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በእስር ላይ የሚገኙ ዜጎች ቁልቁል የፍጢኝ ታስረው የውስጥ እግራቸው እንደሚገረፍ፣ በውሃ ውስጥ እየገቡ እንዲሰቃዩ እንደሚደረግ፣ በእስር ቤት ውስጥ ድብደባ መፈጸምና ለህይወት አስጊ በሆነ እስር ቤት ውስጥ እንዲቆዩ በማድረግ መቅጣት በኢትዮጵያ የተለመደ ነው ብሎአል።ከልካይ የሌለበት የሶማሊ ክልል ልዩ ሚሊሺያም ዜጎችን እንደፈለገ እንደሚገድልና እንደሚያስር፣ በክልሎች ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ልዩ ሚሊሺያዎችም እንዲሁ የኢህአዴግ ባለስልጣናት ጉዳይ አስፈጻሚዎች መሆናቸውን አትቷል።ከሁለት አመት በፊት ባለው አሃዝ በ6የፌደራልና በ120 የክልል እስር ቤቶች ከ70 እስከ 80 ሺ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ወንጀሎች መታሰራቸውን የገለጸው ሪፖርት፣ በይፋ የማይታወቁ በጦር ካምፖች ውስጥ ያሉ እስር ቤቶችንም ዘርዝሯል። ደዴሳ፣ ብር ሸለቆ፣ ጦላይ፣ ሆርማት፣ ብላቴ፣ ታጠቅ፣ ጅጅጋ፣ ሆለታና ሰንቀሌ ስውር እስር ቤቶች ተብለው ተጠቅሰዋል።

የኢድ አል ፈጥር በአልን ለማክበር በስታዲየም ላይ ተገኝተው በነበሩ ሙስሊሞች ላይ መንግስት በወሰደው እርምጃ ከታሰሩት ወደ 1 ሺ ከሚጠጉት ሰዎች መካከል የተወሰኑት በእስር ቤት ውስጥ መሞታቸውንም ሪፖርቱ ጠቅሷል።የሙስሊም ጉዳዮች መጽሄት አዘጋጅ ሰለሞን ከበደ በእስር ቤት ውስጥ ድብደባ እንደተፈጸመበት የጠቀሰው ሪፖርቱ፣ በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ርእዮት አለሙ፣ በ አንዱአለም አራጌ፣ ኦባና ሊሌሳ፣ በቀለ ገርባና ሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ላይ እየደረሱ ያሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዲሁም በሴቶችና ህጻናት ላይ ስለሚደርሱ የመብት ጥሰቶች፣ በአናሳ ጎሳ አባላት ላይ ስለሚደረሰው መፈናቀልና ግጭት በዝርዝር አስቀምጣል። ባለፈዉ ወር የአሜሪካ ምክር ቤት የኢትየጵያ መንግስት የሰብአዊ መብቶች አያያዙን እስከሚያከብር ድረስ የ2014 እርዳታ እንዳይሰጥ ህግ ማውጣቱ ይታወቃል።